# የስድስተኛ ክፍል ሂሳብ የሞዴል ፈተና

## የመለማመጃ ጥያቄ አምስት

1. **60, 75,** እና **105** የጋራ ብቸኛ ትንትን ውስጥ የሚገኙት ቁጥሮች ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

   ሀ) 5 ለ) 3 ሐ) 4 መ) ሀ እና ለ

2. 10፣ 20 እና 30 የጋራ ብቸኛ ትንትን ስንት ነው ?

   ሀ) 3 x 3 ለ) 2 x 5 ሐ) 2 x3 መ) መልስ የለም

3. የ 75፣ 60 እና 105 የብቸኛ የጋራ አብዚዎች ብዛት ስንት ነው ?

   ሀ) 3 ለ) 2 ሐ) 5 መ) 4

4. ሄለን 435 ገጽ ያለውን መጽሃፍ በቀን በቀን በ 25 እና በ 30 መሃከል የሚገኝ ብቸኛ ቁጥርን ያህል ብታነብ መጽሀፉን አንብባ ለመጨረስ ስንት ቀን ይወስድባታል ?

   ሀ) 13 ለ) 12 ሐ) 15 መ) 14

5. ከ 2 እስከ 8 የሚገኙ ብቸኛ ቁጥሮች ት.ጋ.ብ ስንት ነው?

   ሀ. 105 ለ) 30 ሐ. 210 መ. 420

6. ሄኖክ በሚገለገልበት የእስፖርት ማዕከል ውስጥ በየ 6 ቀን ዋና ቢዋኝ፣ በየ 4 ቀን ቢሮጥ እና በየ 16 ቀን ደግሞ ሳይክል ቢነዳ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ከዛሬ ጀምሮ መስራት ቢጀምር በስንተኛው ቀን ላይ ሁሉንም እንቅስቃሴዎች በአንድ ቀን ላይ ሊሰራ ይችላል ?

   ሀ. 18 ለ. 48 ሐ. 32 መ. 26

7. የሚከተሉትን ክፍልፋዮች $\frac{7}{10}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{8}{9}$ ፣ $\frac{11}{3}$ ከትልቁ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ

   ሀ) $\frac{11}{3}$ ፣ $\frac{7}{10}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{8}{9}$ ለ) $\frac{11}{3}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{7}{10}$ ፣ $\frac{8}{9}$

   ሐ) $\frac{8}{9}$ ፣ $\frac{11}{3}$ ፣ $\frac{7}{10}$ ፣ $\frac{3}{4}$ መ) $\frac{7}{10}$ ፣ $\frac{11}{3}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{8}{9}$

8. ከሰፈራችን ወደ ፒያሳ ለመሄድ ሸገር አውቶቡስ በየ 6 ደቂቃ የምትመጣ ሲሆን አንበሳ አውቶቡስ ደግሞ በየ 8 ደቂቃ የምትመጣ ቢሆን ሁለቱም አውቶቡሶች በስንተኛው ደቂቃ በአንድላይ የመጣሉ ?

   ሀ. 45 ለ. 24 ሐ. 42 መ. 56

9. ሳም ለክፍል ጓደኞቹ ለማከፋፈል 39 እርሳሶች እና 26 እስከሪብቶች አሉት? እያንዳንዱ ተማሪ ተመሳሳይ መጠን ያለው እስክሪብቶ እና እርሳሶች መቀበል አለበት እና ምንም እስክሪብቶ ወይም እርሳሶች አይኖሩም. በዚያ ክፍል ውስጥ ከፍተኛው የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

   ሀ. 13 ለ. 54 ሐ. 65 መ. 46

LIVEWORKSHEETS

10. ታሀቱ 36 የሆነ ለ $\frac{5}{6}$ ተመጣጣኝ ክፍልፋይ የሆነው

ሀ) $\frac{25}{36}$ ለ) $\frac{42}{36}$ ሐ) $\frac{30}{36}$ መ) $\frac{72}{36}$

11. የ 273 ብቸኛ ትንትን የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) 3x3x5 ለ) 3x7x13 ሐ) $3^2$ x 5 መ) ሀ እና ሐ

12. 140 በብቸኛ ትንትን ሲገለጽ ________ ነው።

ሀ. $2 \times 3^2 \times 7$ ለ). $\mathbf{2^2 \times 5 \times 7}$

ሐ. $2^3 \times 3^2 \times 5$ መ) $2 \times 5^2 \times 7$

13. 680 በብቸኛ ትንትን ሲገለጽ ________ ነው።

ሀ) 2 x $3^3$ x $5^5$ ለ) $2^3$ x 5 x 17

ሐ) 2 x 3 x $5^5$ መ) $2^3$ x 5 x 11

14. 523ሽ48 በ 9 ተካፋይ የሚሆነው የ "ሽ" ዋጋ ስንት ቢሆን ነው?

ሀ. 5 ለ. 8 ሐ. 7 መ. 9

15. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በ 4 ተካፋይ ነው?

ሀ. 6249 ለ. 7036 ሐ. 225 መ. 915

16. አንድ ቢጫ እና አንድ አረንጓዴ የክሪስማስ አምፖሎች እኩል መብራት ጀምረው ቢጫ አምፖሉ በየ 4 ሴኮንድ የሚ የሚጠፋ ሲሆን አረንጓዴ አምቶል ደግሞ በየ 6 ደቂቃ የበራል ይጠፋል ። ሁለቱም አምፖሎች ለመጀመሪያ በስንተኛው ደቂቃ ላይ እኩል የበራሉ ?

ሀ. 24 ለ. 18 ሐ. 12 መ. 32

17. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንዱ እውነት አይደለም?

ሀ. አንድ ሙሉ ቁጥር በ 8 ተካፋይ ከሆነ በ 4 ተካፋይ ነው ።

ለ. አንድ ሙሉ ቁጥር በ 3 ተካፋይ ከሆነ በ 9 ተካፋይ ነው ።

ሐ. አንድ ሙሉ ቁጥር በ 2 እና በ3 ከተካፈለ በ6 ተካፋይ ነው ።

መ. ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

18. እቤታችን ውስጥ ያሉንን 15 ማንጎዎች፣ 9 ብርቱካኖች እና 18 ሎሚዎች በቅርጫት ውስጥ ለማስቀመጥ ፈለግን ፡፡ ሁሉንም ፍራፍሬዎች ሳናቀላቅል እኩል እኩል በማድረግ በቅርጫቶች ውስጥ ለማስቀመጥ ብንፈልግ በአንድ ቅርጫት ውስጥ ስንት ፍሬዎችን ማስቀመጥ እንችላለን ? ፍራፍሬዎቹን ለማስቀመጥ ጠቅላላ ስንት ቅርጫቶች ያስፈልጉናል ?

ሀ) 5 ፍራፍሬዎችን እና 7 ቅርጫቶች     ለ) 4 ፍራፍሬዎችን እና 16 ቅርጫቶች

ሐ) 3 ፍራፍሬዎችን እና 14 ቅርጫቶች     መ) 3 ፍራፍሬዎችን እና 18 ቅርጫቶች

19. የ 5 ኪሎ ስኳር ዋጋ 133.75 ብር ቢሆን የአንዱ ኪ.ግ ዋጋ ስንት ነው ?

ሀ) 26 ብር     ለ) 26.75 ብር     ሐ) 75 ብር     መ) 668.75 ብር

20. ከሚከተሉት አራት አማራጮች መካከል ልዩ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) %     ለ) 0.01     ሐ) $\frac{1}{10}$     መ) $\frac{1}{100}$

21. ሰላም ከ 30 ሊትር ወተት 4 ኪ.ግ ቅቤ ብታወጣ ከ 90 ሊትር ወተት ምን ያህል ቅቤ ታወጣለች ?

ሀ) 10 ኪ.ግ     ለ) 12 ኪ.ግ     ሐ) 36 ኪ.ግ     መ) 30 ኪ.ግ

22. ( -2, 4) በስርዓተ ውቅር ላይ በየትኛው ሩቤ ላይ ይገኛል ?

ሀ) ሩቤ I     ለ) ሩቤ II     ሐ) ሩቤ III     መ) ሩቤ IV

23. 0.5 + 2 ½ = ...........

ሀ) 4     ለ) 3     ሐ) 75     መ) 5

24. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ) 15 የ 70 አካፋይ ነው     ሐ) 4 የ 124 አካፋይ ነው

ለ) 141 በ 11 ተካፋይ ነው     መ) 20 የ 901 አካፋይ ነው

25. መሬት ከፀሃይ ያላት እርቀት 147,450,000 ኪሎ ሜትር ነው ፡፡ ይህ እርቀት በ 10 ርቢ ሲገለጽ

ሀ) $14.745 \times 10^8$     ለ) $1.4745 \times 10^8$

ሐ) $0.14745 \times 10^8$     መ) $147.45 \times 10^9$

26. 0.213 በመቶ ሲሰላ ስንት ነው ?

ሀ) 21.3 %     ለ) 2.13%     ሐ) 231%     መ) 2130%

27. በሚከተለው መስመራዊ የእኩልነት ዓረፍተ ነገር የተለዋዋጭ ዋጋ ስንት ነው ? በ + 2.25 = 8.75

ሀ) 7.5     ለ) 6.5     ሐ) 8.01     መ) 0.75

LIVEWORKSHEETS

28. 8፣3፣4፣8፣9፣3፣7 ባለ ስንት ሞድ ነው?

ሀ) ባለ 4 ለ) ባለ 1 ሐ) ሞድ የለሽ መ) ባለ 2

29. ከሚከተሉት ውስጥ የጎነ ሶስት እርዝመቶች መሆን የማይችለው የትኛው ነው ?

ሀ) 8 ሳ.ሜ ፣ 6 ሳ.ሜ እና 10 ሳ.ሜ ለ) 7 ሳ.ሜ፣ 5 ሳ.ሜ እና 9 ሳ.ሜ

ሐ) 3 ሳ.ሜ፣ 4 ሳ.ሜ እና 10 ሳ.ሜ መ) 4 ሳ.ሜ፣ 4 ሳ.ሜ እና 6 ሳ.ሜ

30. ከሚከተሉት ውስጥ ጠጣር ምስል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ካሬ ለ) ጎነ ሱስት ሐ) ሲለንደር መ) መልሱ የለም

LIVEWORKSHEETS